# ማዕተብ

**Telegram**
@Deacon_abeselom

**Facebook**
Abeselom Dinkalem

**INSTAGRAM**
deacon_abeselom

**YouTube**
ማዕተብ

**tiktok**
Abeselom Dinkalem




ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥
በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥
በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል
የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።

2ኛ ጴጥ 1:7

# + ተራ የማይደርሰው ተጠማቂ +

**"ከሠላሳ ሰምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ፤ ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እሰከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ፦ ልትድን ትወዳለህን? አለው ሰውዬውም፦ ጌታ ሆይ፥ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውሰጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ሰመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል፡ ብሎ መለሰለት"** ዮሐ5:5-7



ይህንን ጥያቄና መልሰ ሳይ በሸተኛውን ማናገር ያምረኝና እንዲህ በል ይለኛል ፦ እንተ በሸተኛ ግድ የለህም የተጠየቅከውን መልሰ። እመነኝ ጠያቂህ ተራ ጠያቂ ኢይደለም። የሚጠይቅህ ሲያደርቁህ እንደኖሩት አሰልቺ ጠያቂዎች ኢይደለም። ጥያቄውም የሌሎችን ሰዎች ዓይነት ጥያቄ ኢይደለም። ከፊትህ የቆመው የመጠመቂያውን ውኃ ብቻ ሳይሆን በዓለም የሞላውን ውኃ የፈጠረ ነው። "ወደ መጠመቂያው የሚያኖረኝ ሰው የለኝም" አልክን? የተጠየቅከውን መልሰ እንጂ! ወደ መጠመቂያው መግባት ትወድዳለህን? ብሎ ማን ጠየቀህ? ተው እንጂ! የጠየቀህ ማን እንደሆነ ባታውቅ እንኩዋን ጥያቄውን በደንብ ሰማ። ሰው የለኝም እትበለው ፦ ሰለመጠመቂያው ወረፋ እትንገረው ፦ ሰንት ሰው ቀድሞህ እንደዳነ እትቁጠርለት።

የጠየቀህ ግልፅ ጥያቄ ነው።

# ልትድን ትወዳለህን?

እግዚአብሔር ፊት ሰለ ችግርህ ክብደት ለምን ታወራለህ? ምን እንደሌለህማ እሱም ያውቃል። እዎን እድን ዘንድ በለው። ችግርህን ትተህ የምትፈልገውን ንገረው። የችግርህ መወሳሰብና ሥር መሰደድ ለእሱ የሚከብድ ኢይደለምና መዳን እንደምትሻ ብቻ በእምነት ንገረው የሚል ተግሣፅ በበሸተኛው በኩል ወደ እኛ ደረሰ። መጸጉዕ (በሸተኛው) ቤተ ሳይዳ ከመጣ 38 ዓመት ሆነው። ዳዊትና ሰሎሞን 40 40 ዓመት ነግሠው እንኳን ብዙ የምሬት ቅኔ ተቀኝተዋል። ይህ ሰው አልጋ ላይ ሆኖ አርባ ዓመት ሊሞላው ሲል ምንኛ ተንገሽግሾ ይሆን? ልብ በሉ ጌታችን በቤተልሔም ሲወለድ ይህ በሸተኛ

በአልጋው ላይ ነበረ። እረኞች ከብዙ መላእክት ጋር ሲዘምሩ እሱ የአንድን መልአክ መውረድና ውኃውን ማናወጥ እየጠበቀ ሰድሰተኛ ዓመቱን ደፍኖ ነበር። ጌታችን የሠላሳ ሁለት ዓመት ዕድሜ ላይ ደርሶ ወደ መጠመቂያው ሥፍራ ሲመጣም ይህ ሰው አልጋው ላይ ነው። መጠመቂያዋን 38 ዓመት በተሰፋ ሲጠብቅ ቆይቶ ሳይጠመቅባት ቀረ። ጌታ ሆይ የማይደርሰኝን ወረፋ ከመጠበቅ አድነኝ። እንድፈወሰበት ባልፈቀድክበት ሥፍራ ዕድሜዬን እንዳልጨርስ ጠብቀኝ። ወደ ሐዲስ ኪዳንዋ ቤተ ሳይዳ ወደ ቤተክርስቲያን ከመጣሁ ብዙ ዘመን አሰቆጠርኩኝ። ግን እሰካሁንም ድረስ ከኃጢአት አልጋ ላይ አልወረድሁም። መነሣት እፈልጋለሁ ግን አቃተኝ። ልቤ እንጂ እግሬ ጸንቶ መቆም አልቻለም፡ፈረቃ የሌለብህን የሕይወት ውኃ እንተን ሊጠጡ ሲመጡ በዓይኔ እየተቀበልኩ ብዙዎች ጠጥተውህ ሲድኑ በዓይኔ እየሸኘሁ አልጋዬ ላይ ቀረሁ። እኔ እንደተኛሁ ሰንቱ ቀድሞኝ እንደዳነ ባየህልኝ። ከእኔ በጉዋላ መጥተውሰ ከእኔ በፊት ሰንቶች ዳኑ? ሰንቱ ከኃጢአት አልጋ በንሰሓ ተነሥቶ ያንተን ሥጋና ደም ተቀብሎ ተፈወሰ? የቤተ ሳይዳው ሐኪም ሆይ ወደ አንጋፋው በሸተኛህ ወደ ጽኑዕ ሕመምተኛህ ወደ እኔ የምትመጣው መቼ ይሆን? ያን ሕመምተኛ "ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደነበረ" አውቀህ ያናገርከው ሆይ እኔን የምታናግረኝ መቼ ይሆን? እኔሰ ብዙ ዘመን እንደሆነኝ እታውቅምን? ሰው የለኝም : ልብ የለኝም : ኃይል የለኝም : እቅም የለኝም ብዬ ብሶቴን የምነግርህ መቼ ይሆን? "ኢየሱስ፦ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ፡ አለው። ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ" ዮሐ5:8-9 እንተ ተነሥ ብለኸው የማይነሣ ማን ነው? እንኳንሰ ከአልጋ ከመቃብርም ተነሥ ያልከው ይነሣ የለምን? ግዴለህም እኔንም ተነሥ በለኝ። ተነሥ ኃይልን ልበሰ ያልከኝ

እንደሆነ እንኳንሰ "ሸክሜም ቀለል ነው" ያልከው እንተ ያዘዝከኝ የራሴን ሸክም ቀርቶ የወንድሜን ሸክምም ተሸክሜ የእንተን ሕግ እፈጽማለሁ። (ገላ 6:2) "ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ። ... ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና፦ እነሆ፥ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብሰ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ፡ አለው" ይላል። በሸተኛው ድኖ አልጋውን ተሸክሞ እንደሔደ ሳነብ አንድ ነገር ልቤን አሰጨነቀው። ይህ ሰውዬ 38 ዓመት ሙሉ የኖረው በቤተ ሳይዳ ነው። ክርሰቶስ ድንገት ፈውሶት ሒድ ሲለው እሺ ብሎ ከዚያ መጠመቂያ ሥፍራ ከወጣ በኋላ ወዴት ሔደ? የሠላሳ ሰምንት ዓመት ሕመምተኛው ሆይ እውነት ወዴት ሔድህ? ከመጠመቂያው መውጣትህን ሰምተን እድንቀናል። ከዚያስ ወዴት ሔድክ? ዙሪያ ገባው አልተለወጠብህም? መንገድሰ አልጠፋብህም?ወደ ዘመዶች ቤት ሔድክ እንዳልል "ሰው የለኝም" ሰትል ሰምቼሃለሁ። አልጋህንሰ የት አደረሰኳት? መቼም ሰባብረህ እንደማትጥላት የታወቀ ነው። አልጋ ለታመመ ብቻ ሳይሆን ለጤነኛም ያሰፈልጋልና አራት እግር እያላት ጥላህ ያልሔደችውን ዘመድህን መቼም በክብር ማሰቀመጥህ አይቀርም። ለማንኛውም እዚያው ምዕራፍ ላይ ኢየሱስ ይህንን በሸተኛ ዳግም በመቅደስ አገኘው ይላል። ዮሐ 5:14 ጌታ ከመጠመቂያ ቦታ እድኖ ያሰነሣውን ሰው በመቅደስ ቆሞ አገኘው። ይህ በሸተኛ እግሩ ሲጸናለት የሔደው ወደ ፈጣሪ ደጅ መሆኑ ያሰመሰግነዋል። ጌታ በመጠጥ ቤት ቢያገኘው ኖሮ ያሳዝን ነበር። እግርህን ያጸናሁልህ ለዚህ ነው ወይ ብሎ ባዘዘበት ነበር።  አሁን ግን ያዳነው ጌታ በመቅደስ አግኝቶት "እነሆ ድነሀል ከዚህ የሚብሰ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ" አለው።ይህንን የምታነብ ወንድሜ ሆይ ክርሰቶስ እንተንሰ አላዳነህም? "ኸረ እኔ ሸባ ሆኜ አላውቅም። ማንም እኔን ከአልጋ

አላሰነሣኝም ትለኝ እንደሆን እመነኝ ክርሰቶሰ እንደ እንተ ያዳነውሰ የለም። እርሱ እኔና አንተን ተነሡ ብሎ ያሰነሣን ከ38 ሳይሆን ከዙላለም የሲኦልና የኃጢአት አልጋ ነው። እኛን የፈወሰን አልጋችንን አሸክሞ ሳይሆን እሱ ራሱ እኛን ከነአልጋችን ተሸክሞን ነው። ካላመንከኝ ነቢዩ ኢሳይያሰን ጠይቀው "እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ" ሲልህ ትሰማዋለህ። ኢሳ 53:12 የእኛን በደል ተሸክሞ ጀርባው ምን ያህል እንደ ቆሰለ ባየህ። ይህንሰ ጀርባዬን ታያለህ የተባለውን ሙሴን ብትጠይቀው ሳይሻል አይቀርም። ያዳነህ አምላክ አንተንሰ የት ነው የሚያገኝህ? እንደዚህ ሰውዬ መቅደሰ ያገኝህ ይሆን? የትም ቢያገኝህ ግን ቃሉ አንድ ነው "እነሆ ድነሀል ከዚህ የሚብሰ እንዲይደርሰብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ" ከሠላሳ ሰምንት ዓመት የአልጋ ቁራኝነት የሚብሰ ምን ሊመጣ ነው? ካልክሰ እሱን ከማየት ይሠውረኝ ብትል ይሻልሃል።

| ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ | መጋቢት 10 2014 ዓም.| ባሕር ዳር ኢትዮጵያ |

# እናመሰግናለን!

**በእገልግሎታችን ከተደሰታችሁ ምሰጋናን ሁሉጸጠቅልላችሁ ለእግዚአብሔር ሰጡ ።**

ለወዳጆቻችሁያጋሩ

# ማዕተብ

https://t.me/bale_maeteb

abeselomdinkalem78@gmail.com

telegram/facebook/youtube/Instagram